# በኮቪድ-19 (COVID-19 )የድንገተኛ አደጋ ወቅት ከዕዳ ሰብሳቢዎች የሚከላከሉበት መንገድ

**(ሰኔ 3 ቀን 2020 የተሻሻለ)**


በዕዳ ሰብሳቢዎች (debt collector ) ተከሰሼ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ቀነ-ቀጠሮ ተሰጥቶኛል። ምን ማድረግ አለብኝ?

በየግዜው የምከፍላቸውን የብድር ካርድ ክፍያንና ሌሎች ክፍያዎችን ሳልከፍል በመቅረቴ ልከሰስ እችላለሁን

ለመኪና የምከፍለውን ዕዳ መክፈል አቁሜአለሁ ፤ መኪናዬ ትወሰድብኛለችን

የዕዳ ሰብሳቢዎች ከእኔ መውሰድ የሚገባቸውን ዕዳ እንዲወስዱ በእኔ ላይ ላይ ተወስኖብኛል፤ደሞዜን ወይም ባንክ ውስጥ ያለውን ገንዘቤን ሊወስዱ ይችላሉን

መንግስት ወይም ዕዳ ሰብሳቢዎች በኮቪድ-19 ( COVID-19) ምክንያት የሚሰጡኝን የማበረታቻ ገንዘብ ሊወስዱ ይችላሉን

የመብራት፣ የውሃና የጋዝ ክፍያዬን በመክፈል ረገድ ወደኋላ ቀርቻለሁ፤ እነኚህ የየመብራት፣ የውሃና የጋዝ ተቋሞች በዚህ በኮቪድ-19 ( COVID-19)ምክንያት ችግር ለደረሰባቸው ደንበኞች የሚያደርጉት እገዛ አለን

የትምህርት ብድራቸውን ለመክፈል ለማይችሉ ሰዎች የሚደረግ እርዳታ አለን

ያገጠመኝን የገዝብ ችግር ለመፍታት ሊረዱኝ የሚችሉ ምንጮች የትኞቹ ናቸው

ያለብኝን  ዕዳ መክፈል ካልቻልኩ እስር ቤት እገባለሁን

ይሄ የኮቪድ-19 ( COVID-19) በሽታ ካለፈ በኋላ እንዴት ነው ደሞዜ እንዳይቆራረጥብኝ ላድን የምችለው

ይሄ የኮቪድ-19 ( COVID-19) በሽታ ካለፈ በኋላ፤ ባንክ ውስጥ ያለኝ ገንዘብ እንዳይወሰድብኝ ምንድነው ማድረግ ያለብኝ

**በዕዳ ሰብሳቢ ተከስሼ ፍርድ ቤት እንድቀርብ ቀጠሮ አለ። ምን ማድረግ አለብኝ?**

በዚህ በደረሰው የወረርሽኝ በሽታ ምክንያት፤ የዲሲ ከፍተኛው ፍርድ ቤት አስቸኳይ ያልሆኑ የፍርድቤት ቀጠሮዎችን በሙሉ ሰርዞ፤ በስልክ ብቻ የሚደረጉ አዲስ ቀጠሮዎችን እየሰጠ ነው። የበለጠ መረጃ እንድታገኙ ፍርድ ቤቱ ራሱ ከአርሶ ጋር ተገናኝቶ ያስረዳዎታል። ወደ ፍርድቤቱ ዌብሳይት website. በመግባትም ጉዳዮ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለመረዳት ይችላሉ። የፍርድ ቤት ቀጠሮ ከመድረሱ በፊትም የህግ ምክር ማግኘት ይችላሉ። የህግ አገልግሎት ጠበቃም በነጻ ካለምንም ክፍያ ሊያግዞት ይችል ይሆናል።

**የብድር ዕዳዬን (credit card ) ና ሌሎች መክፈል የሚገቡኝ ዕዳዎችን መክፈል አልቻልኩም። ልከሰስ እችላለሁን ?**

- ዕዳ ሰብሳቢዎች የተወሰኑ እንቅስቃሴዎችን እንዳያደረጉ የሚከለክል የአስቸኳይ ግዜ ህግ (emergency law prohibiting certain debt collection activity) በመውጣቱ፤ ገንዘብ አበዳሪዎችና ዕዳ ሰብሳቢዎች፤ በዚህ በዲሲ የህዝብ የአስቸኳይ የጤና ቀውስ ግዜ እና ቀውሱ ካለፈ በኋላ ላሉት 60 ቀናት፤ አዲስ ክሶችን እንዳይመሰረቱ ተከልክለዋል። ይህ የእገዳ ግዜ ካልተሰረዘ ወይም እንዲራዘም ካልተደረገ በስተቀረ **መስከረም 22 ቀን 2020** ያበቃል።.

- የዕዳ ሰብሳቢዎች መቼና እንዴት ከእርስዎ ጋር እንደሚገናኙ ገደብ አለው፤ እርስዎ ግን በማንኛውም ግዜ ከአበዳሪዎችዎ ጋር ለመገናኘት ፍቃድ አሎት ለምሳሌ እርሶ ከፈለጉ፤ አንድ ዓይነት የአከፋፈል ሁኔታ ለማመቻቸት ደውለው ሊነጋገሩ ይችላሉ። ብዙ አያሌ ገንዘብ አበዳሪዎችም፤ ችግር ውስጥ በማለፍ ላይ ያሉ ደንበኞቻቸው፤ በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) የቀውስ ግዜ ሊረዱበት የሚችሉ አያሌ ፖሊሲዎችን ማውጣታቸውን አውጀዋል።

**ለመኪናዬ የምከፍለው የነበርኩትን ክፍያ ለማቆም ተገድጃለሁ። መኪናዬን መልሰው ሊወስዱብኝ ይችላሉን ?**

- በዚህ በህዝብ የጤና ቀውስ ወቅትና ከዛም በኋላ ለሚቀጥሉት 60 ቀናት፤ አበዳሪዎች መኪናዎን መልሰው ለመውሰድም ይሁን እንወስደዋለን እያሉ ማስፈራራም አይችሉም።

- ይህ ግዜ ከተገባደደ በኋላ( እስከአሁን ድረስ ቀኑ መስከረም 22 ቀን 2020 ነው)፤ መኪናዎ ሊወሰድቦ ይችላል። መኪናዎ ተወስዳ ከተሸጠች በኋላ፤ የተሸጠችበት ዋጋ ዕዳዎን የማይሸፍን ከሆነ በዕዳዎና በሽያጩ ዋጋ መካከል ያለውን ልዩነት የመክፈል ሃላፊነት ያሎት እርስዎ ሊሆኑ ይችላሉ።

- በርካታ አበዳሪዎች፤ በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት የገንዘበ ችግር ላጋጠማቸው ደንበኞቻቸው አንድ ዓይነት መፍትሄ እያደረጉ ነው። አዲስ የአከፋፈል ሁኔታ እንድታገኙ ከአበዳሪዎችዎ ጋር ተገናኘተ ተወያዩ።

**የዕዳ ሰብሳቢዎች ባቀረበብኝ ክስ ምክንያት በላዬ ላይ የፍርድ ቤት ውሳኔ ተወስኖብኛል። ደሞዜን ወይም በባንክ ያለኝን ገንዘብ ሊወስዱብኝ ይችላሉን?**

በዚህ በህዝብ የጤና ቀውስ ወቅት ከዛም በኋላ ለ60 ቀናት (ቀኑ የሚያልቀው መስከረም 22 ቀን 2020) ገንዘብ አበዳሪዎችና እዳ ሰብሳቢዎች፤ የደሞዝ መቁረጥ ወይንም ከባንክ ገንዘቦን የመውሰድ አዲስ ጉዳይ ሊያነሱ አይችሉም።ይሁንና፤ ቀደም ሲሉ የተደረጉ የደሞዝ መቁረጥ ውሳኔዎች እንዳሉ በቦታቸው ይቆያሉ። በዚህ በሚቆረጥ ደሞዝዎም ሆነ ከባንክ በሚወሰድ ተቆራጭ ገንዘብ ግን ችግር ካለቦት የጠበቃ እርዳታ ይጠይቁ።

**መንግስት ወይም የዕዳ ሰብሳቢዎች በኮቪድ-19 (COVID-19 )ምክንያት የሚሰጠንን የማበረታቻ ክፍያ ሊወስዱ ይችላሉን?**

- ማእከላዊው መንግስት፤ ያለቦትን የግብር ዕዳንም ሆነ ያለተከፈለ የትምህርት ብድሮን ለመክፈል መንግስት ራሱ ከሚሰጦት የማበረታቻ ክፍያ ሊወስድ ወይም ሊቆርጥ አይፈቀድለትም። ይህ ግን በራስዎ ላይ ከደረሰ፤ ህጋዊ ምክር ለማግኘት እርዳታ ጠይቁ።ይሁንና፡ አሁን ባለው ህግ መሰረት፤ መክፈል የሚገባዎትን የልጆችዎን ማሳደግያ ገንዘብ (child support) ካልከፈሉ፤ መንግስት የማበረታቻ ገንዘቦን ይህንኑን ለመክፈል ሊያውለው ይችላል።

- በዲስትሪክቱ፤ ዕዳ ሰብሳቢዎችም ሆኑ ገንዘብ አበዳሪዎች፤ ይህ ኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ እስካለ ድረስና ከዛም በኋላ ለሚቀጥሉት 60 ቀናት( እስከ መስከረም 22 ቀን 2020) በባንክ ውስጥ ያለን ገንዘብንም ሆነ ሌላ ንብረት የዕዳ መክፈያ ብለው ሊይዙ አይችሉም። አያሌ ሰዎችም፤ የተሰጣቸውን የማበረታቻ ክፍያን እስከዛን ግዜ ድረስ ተጠቀመው ይጨርሱታል)።

**የመብራት፣የውሃና የጋዝ ክፍያዬን መክፈል አልቻልኩም። በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ችግር ላይ ለወደቁ ሰዎች ምን የሚያደርጉት ነገር አለ?**

በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19)ወቅትና ከዛም በኋላ ለ15 ቀናት (ይህም እስከ ነሃሴ 8 ቀን 2020 ድረስ ማለት ነው) የመብራት፣ የውሃ፣ የጋዝ፣ የኬብል ወይም የስልክ ተቋሞች፤ ዕዳ አልከፈላችሁም ብለው ማንኛውንም ነገር መቁረጥ አይችሉም። በተጨማሪም፤

- ዋሽንግተን ጋዝ (Washington Gas) የመክፈል ግዜ ላሳለፉ ሰዎች ሲያደርገው የቆየውን ክፍያ( late fees) አንስቶታል። ላልከፈሉ ሲያደርገው የቆየውን የአገልግሎት ማቋረጥንም ለግዜው በይቆይ ይዞታል።

- ፔፕኮ (Pepco) የመክፈል ግዜ ላሳለፉ ሰዎች ሲያደርገው የቆየውን ክፍያ( late fees) አንስቶታል። የአገልግሎት ማቋረጥንም በይቆይ ይዞታል።

- የዲሲ የውሃ አገልግሎት ዲሲ ዋተር (DC Water) የውሃ አገልግሎት እንዳያገኙ የውሃ መስመር ቆርጦባቸው የቆዩን ሰዎች የውሃ መስመራቸውን እንደገና እያገናኘ ነው።

ለተጨማሪ መረጃ ከተቋሞቹ ጋር ተገናኙ።

የመብራት፤ የውሃ ወይም የጋዝ ክፍያዎን ለመክፈል ችግር ላይ ካሉ፤ ምናልባት አነስተኛ ገቢ ላላቸው የሚደረግ የመብራት/ኤለክትሪክ እርዳታ (Low Income Energy Assistance Program (LIHEAP) ወይም (Utility Discount Program) እገዛ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚሁ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፤ ወደ መንግስት የኤነርጂና የአካባቢ ሚኒስቴር ዌብሳይት ውስጥ https://doee.dc.gov/liheap ይግቡና ይመልከቱ።

በመብራት፣ ውሃና ጋዝ ስለሚደረጉ ማጭበርበርያዎች ማስታወሻ፤ ከፔፕኮ ነኝ የሚል ወይም በአነስተኛ ዋጋ አገልግሎት ከሚሰጥ ተቋም ነኝ የሚል የስልክ ጥሪ ካገኙ፤ ይህ የማጭበርበርያ ጥሪ ሊሆን ይችላል። ተጭበርብሬአለሁ የሚል እምነት ካሎት፤ ወደ ሜትሮፖሊታን የፖሊስ ጣብያ የገንዘብና የሳይበር ወንጀል ክፍል (Metropolitan Police Department's Financial and Cyber Crimes Unit) ጋር በስልክ ቁጥር 202-727-4159 በመደወል ወይም በኦንላይን mpd.fraud-unit@dc.gov ውስጥ በመግባትና ወደ ኦ-ኤ ጂ የገበያተኛ ጥበቃ ክፍል (OAG's Office of Consumer Protection) በስልክ ቁጥር (202) 442-9828 በመደወል፤ በኦንላይን ወደ ሚገኘው consumer.protection@dc.gov በመግባት አቤቱታ ያቅርቡ። ወይም የገበያተኛ ቅሬታ ፎርም(online consumer complaint form) ይሙሉ። ስለነዚህ ዓይነቶቹን ጥሪዎች ጥሪዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ካስፈለጎ https://oag.dc.gov/blog/consumer-alert-covid-19-pepco-scam ን ይጎብኙ።

## የትምህርት ብድር መክፈል ላልቻሉ ሰዎች የሚደረግ እርዳታ አለን?

በማእከላዊው መንግስት የኬርስ ህግ CARES Act መሰረት፤ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የሚከፈሉ የትምህርት ዕዳዎች ሁሉ ከመጋቢት 13 ቀን 2020 ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2020 ድረስ በይቆይ ተይዘዋል፤ የሚከፈለውም ወለድ 0% ነው። ለዚሁ ዓይነት ጠቀሜታ የእርስዎ ክፍያ ብቁ መሆኑንና አለመሆን ከተጠራጠሩ፤ የብድር አገልጋዮን ጋ በቀጥታ ደውለው ይጠየቁና ያረጋግጡ። አገልጋዮ ማን እንደሆነ የማያስታውሱ ከሆነ ደግሞ ወደዚህ the Federal Student Aid site ይግቡወይም በስልክ ቁጥር 1-800-4-FED-AID በመደወል ያረጋግጡ። ሌላ አዲስ ነገር ካለ ደግሞ ወደ Federal Student Aid's official coronavirus page ይግቡና ያረጋገጡ።

የሚከፈል የትምህርት ዕዳ ካለቦት፤ If you have a qualifying federal student loan:

- ምንም ነገር ማድረግ የለቦትም ምክንያቱም ለግዜው በይቆይ ተይዟልና
- **ከመጋቢት13 ቀን 2020** በኋላ የከፈሉት ነገር ቢኖር፡ የከፈሉት እንዲመለስልዎ ከአገልግሎት ሰጪዎ ጋር ተገናኙ።

- በዚህ ወቅት ብድሮች ወለድ አይያዝባቸውም፡ ከፈለጉ ወደ ዋናው ብድር የሚያመራ ክፍያ (principal-only) ሊያደርጉ ይችላሉ።

- በዚህ በተጠበቀ ግዜ ከደሞዝ የሚቆረጥ የለም፤ ከግብር የሚወሰድ ገንዘብ የለም፤ ከመንግስት ከሚሰጡ ጠቀሜታዎች የሚቀነስ የለም፤ ወይም የሚደረግ የዕዳ ስብስባ ተግባር ማካሄድ አይፈቀድም። በትምህርት ሚኒስቴር በዚህ በተከለከል ግዜ፤ አያሌ ከደሞዝ እየተቆረጠ የሚደረጉ ክፍያዎች እንደተደረገ በተለላፉ መረጃዎች ሊታወቅ ተችሏል። ይህ በሺዎች በሚቆጠሩ አሜሪካኖች ላይ የደረሰ ቢሆንም፤ በእርሶ ላይ ከደረሰ ህጋዊ እርዳታ ፈልጉ።

ይህ የፋታ ማግኘት እርምጃ ( relief) በፐርኪንስ ብድርና( Perkins Loans) ና በማእከለዊው መንግስት የቤተሰብ የትምህርት ብድር( Federal Family Education Loans) በባንኮች ወይም ዋስትና ሰጪ ተቋሞች አይመለከትም።.

**ያጋጠመኝን የገንዘብ ችግር ለማቃለል የሚረዱኝ ምንጮች እነማን ናቸው?**

- በካቶሊክ ቻሪቲስ (Catholic Charities) የሚካሄደው ገንዘባዊ መረጋጋት ኔትወርክ (Financial Stability Network)፤አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦችና ግለሰቦች ነጻ ገንዘባዊ ምክር፤ የግብር እገዛ ያደርጋል።ስለዚሁ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ በ website ይግቡ ወይም በስልክ ቁጥር (202) 772-4300 የውስጥ መስመር 153 ይደውሉላቸው።

- የመላው አገሪቱ የገበያተኛ ህግ ማእከል (The National Consumer Law Center) ለገበያተኞች Surviving Debt የሚል ጽሁፍ አላቸው (በዚህ በኮሮናቫይሩስ ወቅት ነጻ ነው)

ይሄው የጤና ቀውስ ካለቀ በኋላ፡ ኪሳራ ያገጠማቸውና ኪሳራ እንዳጋጠማቸው ለፍርድ ቤት ማሳወቅ የሚፈልጉ ሰዎችን የሚጠቅሙ ምንጮች:

- የኪሳራ እርዳታ ማእከል (Bankruptcy Assistance Center) (በማእከላዊው መንግስት የኪሳራ ፍርድ ቤት ድጋፍ የሚካሄድ )

- የዲሲ የህግ ምክርና ሬፈራል ክሊኒክ (D.C. Bar Advice and Referral Clinic)

**ዕዳዬን ባልከፍል እታሰራለሁን?**

አይታሰሩም። ዕዳ ባለመከፈልዎ ብቻ አይታሰሩም።

**ይህ የወረርሽኝ በሽታ ካለፈ በኋላ፤ ደሞዜ እየተቆራረጠ እንዳይወሰድ እንዴት ነው የምከላከለው?**

በዚህ በህዝብ ጤና ቀውስ ውስጥ በምንገኝበት በአሁኑ ወቅትና ችግሩ ካለፈ እስከ 60 ቀናት ድረስ፤ ገንዘብ አበዳሪዎች፤ ከደሞዝ እየተቆረጠ ይሰጠኝ የሚል ጥያቄ ለፍርድ ቤቶች ሊያቀርቡ አይችሉም።የተመደበው ግዜ ካለቀ በኋላ፡ በእርስዎ ላይ አንዳች ቅሬታ ካላቸው ሊያቀርቡ ይችላሉ። ግን አሁን ባለው የዲሲ ህግ፤ በሳምንት ከሚቀበሉት ደሞዝ  ቤትዎ ከሚወስዱት እስከ $560 በሳምንት የሚደርስ ገንዘብ አይነካቦትም። ከዛ በላይም ቢያገኙ ባለው ችግር ምክንያት የሚቆረጥቦትን ፍርድ ቤቱ እንዲያሻሽልሎት የመጠየቅ መብት አሎት። የሚከተለውን ፎርም Motion to Exempt Wages from Garnishment and Request Hearing መሙላት አለቦት።ይህ ፎርምም በጽሃፊው መስርያ ቤት (Clerk's Office) ሊያገኙት ይችላሉ ወይም በሚከተለው የፍርድ ቤቱ ዌብሳይት https://www.dccourts.gov/services/formsበመግባት "Motion to Exempt Wages."በሚል አርእስት ስር ሊያገኙት ይችላሉ።

**ይህ የወረርሽኝ ግዜ ካለፈ በኋላ፤ በባንክ ያለኝን ገንዘብ እንዳይወሰድ እንዴ ነው የምጠብቀው?**

በዚህ በያዝነው የወረርሽኝ በሽታ ወቅትም ሆነ ከዛ በኋላ ባሉት 60 ቀናት፤ አበዳሪዎች በባንክ ውስጥ ያሎት ገንዘብ እንዲያዝ ወይም ከዛ ወጥቶ እንዲከፈላቸው ፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲሰጥ ክስ ማቅረብ አይችሉም። ያ የተወሰነው ግዜ ከተገባደደ በኋላ፤ ገንዘብ አበዳሪዎ፤ በሶ ላይ አንዳች አሉታዊ ነጥብ ካለው፤ ባንክ ያሎትን ገንዘብ እንዳያወጡና ከዛም በኋላ ያለቦት ዕዳ ገንዘብ ከባንክ ተወስዶ፤ ያለቦት ዕዳ እንዲከፈል ፍርድ ቤቱ እንዲያደርግ ሊጠይቅ ይችላል። አበዳሪዎ፤ የትእዛዙን ኮፒ ወይም ቅጂ በፖስታ እንዲልክሎት ይጠየቃል፤ ይህም ሪት(writ) ይባላል። በተጨማሪም ወረቀቱን ለባንክ በሰጠ በሶስት ቀናት ውስጥ ማስታወሻ ለእርዎ መላክ አለበት። በባንክ ውስጥ ያሉ እንደ ሶሻል ሴኩሪቲ (Social Security) ወይም የኤስ-ኤስ አይ(SSI) ክፍያዎች፤ ከእነዚህ ዓይነቶች ተቆራጮች የተጠበቁ ናቸው፤ ነጻ ለመሆንም የሚያስችሉ ሌሎች መንገዶች አሉ።ባንኩ ያሎት ገንዘብ እንዳይነካ Motion for Claim of Exemption የሚባለውን ፎርም በመሙላት ፍርድ ቤቱ ገንዘቡ እንዳይወሰድ እገዳ እንዲያደርግ መጠየቅ ይችላሉ።

***

ስለ ሁኔታዎ የህግ ምክር ቢያስፈልጎ፡ ከሊጋል ኤድ( Legal Aid) ጋር ተገናኙ። በኖርትዌስት (Northwest)ና በሳውትዌስት( Southeast) የሚገኙት መስርያ ቤቶቻችን ለህዝብ ተዘግተዋል። ግን በስልክ ወይም በኦንላይን ልታገኙን ይችላሉ። አገልግሎታችንን ማግኘት ከፈለጉ በስልክ ቁጥር (202) 628-116  ወይም በ online ገብተው ማመልከት ይችላሉ።